# ቆሜነው እምሞተው !!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

አልጠብቅም ሞትን ተኝቼ ባልጋዬ ፤
እኔው እሄዳልለሁ ፈረሴን ቼ ! ብዬ ፤
አልፈልግም ዋሻ የምደበቅበት ፤
አልፈልግም ጢሻ የምሸሸግበት ፤
አልሰብርም አንገቴን አላዞር ግንባሬን ፤
አይዝልም ጉልበቴ አላጥፈውም ክንዴን ፤
እጠብቀዋለሁ ደረቴን ነፍቼ ፤
በኩራት በድፍረት አንገቴን አቅንቼ ፤
አልንበረከክም ቆሜነው እምሞተው ፤
የጀግና ልጅ ጀግና መሆኔን ይወቀው !!

በንባ አልታጠብም ቁጭብዬ አላለቅስም ፤
ጉልበቴን አጥፌ አልንበረከክም ፤
አልጠብቅም እሱን ወደኔ እስቲመጣ ፤
እኔው እሄዳለሁ ወደሱ እንዳይመጣ ፤
ኩራቴን ይረዳው ድፍረቴን ይወቀው ፤
ተጋድሜ አልሞትም ቆሜነው እምሞተው !!

አልጠብቅም ሞትን ማታ በጨለማ ፤
እንዲወስደኝ ብዬ ሰው ሳያይ ሳይሰማ ፤
አለምንም ክቶ ዛሬን እንዲተወኝ ፤
ዘግይቶ እንዲመጣ ዕድሜ እንዲለግሰኝ ፤
ወይ እንደባለጌ እያምላቀቀ ፤
ሞት መጥቶ እስቲወስደኝ እያጨማለቀ ፤
ጭራሽ !
እጠብቀዋለሁ በጠራራ ፀሐይ ፤
መሃላዬ ይሁን ቃል ለምድር ለሰማይ ፤
ዳግም ድል አድርጌ እስክነሳ ድረስ ፤
ቆሜነው እምሞተው እንደ ክርስቶስ ::

ይለግሰኝ ብዬ ትርፍራፊ እድሜ ፤
አልጠብቅም ክቶ እኔ ተጋድሜ ፤
እሄዳለሁ እኔ ወደሱ እንዳይመጣ ፤
ግንባሬን አላጥፍም የመጣው ቢመጣ ፤
ተኝቼ አልጠብቅም ሞት መጥቶ እስቲወስደኝ ፤
እኔው እሄዳለሁ በቁሜ እንዲያገኘኝ ፤
ለመኖር ጓጉቼ አልንበረከክም ፤
ዛሬን ተወኝ ብዬ አልለማመጥም ፤
አልንበረከክም ቆሜነው እምሞተው ፤
የጀግና ልጅ ጀግና መሆኔን ይወቀው !!

ጥቅምት 9 ቀን 2002 ዓ.ም. (october 19 2009)

ለወይዘሪት ብርቱካን ሚደግሳና አበራሽ በርታ እንዲሁም ለሌሎች የሕሊና እስረኞች ወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ::